DEPARTMENT OF LABOR AND INDUSTRY

# ነፍሰጡርና የሚያጠቡ እናት ሰራተኞች የሚያስፈልጓቸውን መገልገያዎች የማቅረብ መግለጫ

የሚኖሶታ ነፍሰጹር ሰራተኞችንና  የሚያጠቡ እናቶችን የሚያስተናግዱ ህጋዊ መብቶች  (የሚኖሶታ ህጎች 181.939- Minnesota Statutes § 181.939)

ነፍሰጡር ሰራተኞች ምክንያታዊ የሆኑ የተወሰኑ አገልግሎቶች እንዲቀርቡላቸው የመጠየቅና የማግኘት መብት አላቸው። እነኚህ መብቶች በሚከተሉት ላይ ብቻ የተወሰኑ ሳይሆኑ፤ የሚከተሉትን የሚያጠቃልሉ ናቸው፤ ቶሎ ቶሎ እረፍት የማግኘት ወይም ረዘም ያሉ እረፍቶችን የማግኘት መብት፣ ቁጭ ብሎ የመስራት መብት፣ የሚሸከሟቸው ዕቃዎች ክብደት የተወሰነ የመሆን መብት፣ ወደ ሌላ ቦታ በግዜያውነት የመዛወር መብት፣ ግዜያዊ ከስራ መቅረት ወይም የስራ ወይም የስራ ሰዓታት የመስተካከል መብት። አስሪ፤ ማንኛውም ሰራተኛ የስራ ፈቃድ እንዲወስድ ወይም የሆነ ዓይነት የተደረገለትን ማስተካከያ እንዲቀበል መጠየቅ አይችልም።

የሚያጠቡ እናቶች፤ የሚከፈሉበት መደበኛ የእረፍት ግዜያቸውን ለምሳሌ የምሳ ሰዓታቸውን መጠቀም ካልፈለጉ በስተቀረ፤  ወተት ከጡት ጨምቆ ለማስቀመጥ ደሞዝ የሚከፈልበት፣ አመቺ የሆነ የእረፍት ግዜ የማግኘት መብት አላቸው። አሰሪዎች፤ ንጽህናው የተጠበቀ፣ጸጥ ያለና ደህንነቱ የተጣራ እንዲሁም የወተት ማለብያ መሳሪያቸውን ለመሰካት የሚያስችላቸው የኤሌክትሪክ ግንኙነት ያለውና ከስራው ቦታ አጠገብ የሚገኝ፣ መታጠብያ ቤት ያልሆነ ክፍል ሊመደቡላቸው ያስፈልጋል።

በዚህ ህግ መሰረት መብታቸውን በመጠቀም ላይ በሆኑ የሚያጠቡ እናቶች ወይም ነፍሰጡር ሰራተኞች ላይ የበቀል እርምጃ ወይም ማንኛውንም አሉታዊ እርምጃ መውሰድ በህግ የሚያስጠይቅ ነው።

በህጉ መሰረት መብቴ ተጥሷል የሚሉ ሰራተኞች፤ የሚኖሶታ የስራና የኢንዱስትሪ መምርያ የስራ ደረጃ ክፍል (Minnesota Department of Labor and Industry’s Labor Standards Division) ጋር በኦንላይን ወደ dli.laborstandards@state.mn.us በመግባት ወይም በስልክ ቁጥር 651-284-5075 በመደወል እርዳታ ማግኘት ይችላሉ። በተጨማሪም መፍትሄ ለማግኘት በህጋዊ መንገድም ክስ ሊያቀርቡ ይችላሉ። ስለዚሁ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ወደ dli.mn.gov/newparents.ገብተው ይመልከቱ።